# የቅጣት አወሳሰን ስልጠና ሞጁል

## ማውጫ

1. የቅጣት መሰረታዊ አላማዎችና መርሆዎች ........ 3
1.1. የቅጣት አላማና ግብ፣ ........ 3
1.2. የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች፣ ........ 6
2. የቅጣት ምንነትና የቅጣት አይነቶች፣ ........ 7
3. ስለቅጣት አወሳሰን የወንጀል ህጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣ ........ 16
3.2. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች ........ 20
3.3. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ........ 22
3.4. ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ........ 27
4. በጥፋተኛው ላይ ለጊዜው ጥፋት አለመጣልና በገደብ ስለመልቀቅ፣ ........ 28
4.1. ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ ቅጣት አለመጣል (ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት) ........ 28
4.2. ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ ........ 29
5. የቅጣት አወሳሰን ላይ የሚታዩ ችግሮች፣ ........ 32
6. የቅጣት አወሳሰን የታሰበውን ግብና አላማ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ተግባራት፣ ........ 37
ዋቢ ሰነዶች፣ ........ 38

## የስልጠናው አጠቃላይ አላማዎች

ይህን ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞቹ፡-

1. የቅጣት አወሳሰን በህጉ መሰረት መሆን እንዳለበት ይገነዘባሉ፡፡

2. የቅጣት አሰጣጥ ስነስርአቱንም ይለያሉ፡፡

## ዝርዝር አላማዎች፣

ሰልጣኞች ይህንን ስልጠና ሲያጠናቅቁ፣

1. ስለቅጣት ምንነትና አይነቶች ያላቸው እውቀት ይዳብራል፡፡
2. የቅጣት አላማዎችና ግቦች ላይ ያላቸው እውቀት ይዳብራል፡፡
3. የቅጣት አላማዎችና ግቦችን ለማሳካት መሰረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤና መረዳት ይጨምራል፡፡
4. በወንጀል ህጉ ስለቅጣት አወሳሰን በተደነገጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ ይዳብራል፡፡
5. በአገራችን የቅጣት አወሳሰን ላይ ስላሉት ችግሮችና የችግሮቹ መንስኤ ተመሳሳይ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
6. የወንጀል ፍርድ ከተሰጠ በኃላ የቅጣት አወሳሰን ስነ ስርዓትን ይለያሉ፡፡
7. የቅጣት አሰጣጥ ስነስርአት ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡
8. ግራ ቀኙን በአግባቡ ማዳመጥና ማስረጃዎችን መስማት የሚገባ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡
9. የቅጣት ውሳኔ ምክንያት ሊቀመጥለት የሚገባ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡

# 1. የቅጣት መሰረታዊ አላማዎችና መርሆዎች

## 1.1. የቅጣት አላማና ግብ፣

የቅጣት መሠረታዊ ዓላማዎች ምንድን ናቸው? የቅጣት መሰረታዊ ዓላማዎችን ማወቅ ለምን ያስፈልጋል?

ቅጣት ለቅጣት ተብሎ የሚወሰድ እርምጃ ሳይሆን አላማና ግብ አለው፡፡ በኢትዮጵያ የቅጣት መሠረታዊ ዓላማዎችና ግቦች ምን ምን ናቸው የሚለውን ለመረዳት የኢትዮጵያ

ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ የመጀመሪያውን አንቀጽ ድንጋጌ በጥንቃቄ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የድንጋጌው የአማርኛ ቅጂ እንደሚከተለው ይነበባል፡-
የቅጣት አላማና ግብ ምንድነው? የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ የመጀመሪያው አንቀጽ ድንጋጌ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፡፡

"አንቀጽ 1 .ዓላማና ግብ

የወንጀል ሕግ ዓላማ፣ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦችን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" ይላል፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እንደምንገነዘበው የወንጀል ሕጉ ዓላማ የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦቿንና የነዋሪዎቿን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ሲሆን ይህ የሚደረገውም ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ አላማውን ለማሳካት እንደግብ አድርጎ የያዘው ወንጀል እንዳይፈፀም የመከላከል ተግባር ሲሆን፣ ይህንንም ለማሳካት ሁለት ስልቶችን ወይም ስትራተጂዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ያስቀምጣል፡፡ አንደኛው ከምንም በፊት ሕብረተሰቡ በወንጀልነት የተፈረጁ ድርጊቶችንና የሚያስከትሉትን ቅጣት አስቀድሞ እንዲያውቅ በማድረግ ከእነዚህ የወንጀል ድርጊቶች እንዲቆጠብ ማድረግ ነው፡፡

አንድ ድርጊት ሕገ ወጥ መሆኑና በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አስቀድሞ እንዲታወቅ ካልተደረገ ወንጀል የሕብረተሰቡን ጥቅም የሚጻረር ድርጊት ስለመሆኑ ካለው

አጠቃላይ ግንዛቤ አንጻር ይህን ግንዛቤ በመውሰድ ራሳቸውን የሚጠብቁ ሊኖሩ ቢችሉም አንድ ድርጊት ወንጀል ነው አይደለም የሚለው ጉዳይ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ውሳኔ የተተወ ስለሚሆን ሰዎች የወንጀል ድርጊቶች ተብለው የተፈረጁትን ጉዳዮች አስቀድመው አውቀው ድርጊቶቹን ከመፈፀም እንዲቆጠቡ አያስችላቸውም።

ሁለተኛው ስልት ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን መቅጣት ነው። የተከለከሉ ድርጊቶችና ቅጣታቸው አስቀድሞ እንዲታወቅ ቢደረግም በየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ውስጥ ክልከላውን ተላልፈው የወንጀል ድርጊቶችን የሚፈፅሙ ሰዎች ይኖራሉ። በመሆኑም የወንጀል ሕጉ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በማክበር እንቅስቃሴያቸውን አስተካክለው ከተከለከሉ ድርጊቶች ራሳቸውን ያላራቁ ሰዎች ሲገኙ ተገቢው ቅጣት በመቅጣት አጥፊዎች ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ነው።

በዚህም መሰረት የወንጀል ሕጋችን የወንጀል ድርጊት በፈፀሙ ሰዎች ላይ ቅጣት እንዲጣል ማድረግን በራሱ ግብ አድርጎ አይወስደውም። በአጥፊዎች ላይ ቅጣት የሚጣለው በቅጣቱ አማካኝነት በዋናነት ሦስት ዓላማዎችን ለማሳካት ነው። እነርሱም መቀጣጫ እንዲሆኑ (deterrence)፣ ወንጀል እንዳይፈጽሙ መከላከል፣ (prevention, incapacitation, disabling)፣ ማረም (reformative, rehabilitative) ናቸው። ይህም የመጨረሻ ግቡና ውጤቱ ወንጀል በቀጣይነት እንዳይፈጸም መከላከል ነው።

***<u>የመወያያ ጥያቄዎች፡-</u>***

1. በመ.ቁ. 51889 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 (3) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሁለት ሰዎች በመግደልና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በሁለት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት በማድረስ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በሚከተለው ዓይነት ወስኗል፤

   "ቅጣት መወሰን ያለበት ለማስተማር ለማረምና የተቀጪውን መሰሎች ጨምሮ ለማስጠንቀቅ ነው፤ እንዲሁም ቅጣት ሲሰጥ በወንጀል ሕግ ቁጥር 88(2) ላይ የተዘረዘሩትን ምክንያቶች በማመዛዘን ነው። ስለዚህ ከላይ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በማለት የተጠቀሱትን በማገናዘብ … ተካሳሹ ጥፋተኛ ከተባለበት መነሻ

በመውረድ በሁለት ዓመት እስራትና በብር አስር ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 149(5) መሠረት ፈርደናል” ይላል፡፡

- የቅጣት ውሳኔው በእርግጥም የቅጣት ዓላማዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው ማለት ይቻላል?

2. በተመሳሳይ ወይም በአንድ ቅጣት በአንድ ጊዜ ሁሉንም የቅጣት ዓላማዎች ማሳካት ይቻላል? ወይስ የትኛው የቅጣት ዓላማ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንደሚኖረው በመመዘን ያን ዓላማ የሚያሳካ ቅጣት መጣል ይኖርበታል?
3. የተለያዩ የቅጣት ዓይነቶች በወንጀል ሕጋችን ተካተዋል፡፡ እነዚህ ቅጣቶች በውስጣቸው የሚሰጡት የቅጣት ዓላማ ፍንጭ ምን እንደሆነ እንመርምር፡፡

## 1.2. የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች፣

ቅጣት በተገቢው መልኩ የታለመለትን ግብና ውጤት ያሳካ ዘንድ ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች አሉ፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **ወጥነት**/consistency/፡- ወንጀል ግላዊ ባህሪ ያለዉ በመሆኑ የአንዱ ምክንያት ለሌላዉ የሚተላለፍ አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን ወጥ በሆነ መልክ ተመሳሳይ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮች አንፃራዊ ልዩነቶች ተጠብቀዉ ተቀራራቢ የሆነ ዉሳኔ ሊወሰንባቸዉ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ በሆኑ ወንጀሎች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣቶችን መጣል አንዱ ሊከበር የሚገባው መርሆ ነው፡፡ ለእኩል ጥፋት እኩል ቅጣት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባልና፣
2. **ተመዛዛኝነት**/proportionality/፡- ሁሉም ወንጀሎች በሚያደርሱት ጉዳት፣ በወንጀሉ አደገኛነት፣ የአጥፊው የአእምሮ ሁኔታ፣የጥፋተኛው ያለፈ የወንጀል ታሪኩን በማገናዘብ እንደሁኔታው ቅጣቱ ከድርጊቱ ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን እንደሚገባ የሚያሰምር መርህ ነው፡፡ ስለሆነም የቅጣት መጠን እንደወንጀሉ ክብደት ማለትም አደገኛነት፣ ያደረሰው ጉዳት፣ ወዘተ ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡
3. **ግልፅነት**/Transparency/:- ግልፅነትና ተጠያቂነት አብረዉ የሚሄዱ መርሆዎች ናቸዉ፡፡ ዳኞች ዉሳኔቸዉን በምክንያት ማስደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ዳኞች ወደአንድ የቅጣት ውሳኔ የደረሱበትን ምክንያት በግልጽ እንዲያስቀምጡ ማድረግ አወሳሰኑ በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን

ለመገምገም እንዲሁም ለመማርም የሚያስችል ነው። ቅጣት በግልጽ ከነምክንያቶቹ ሲቀመጥ ሌሎች የህብረተሰበ አካላትም በግልጽ አይተዉት መገመት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ማለት ነዉ። የግልፅነት መርሆዉ የዳኞችን የተጠያቂነት አድማስንም ያሰፋል ማለት ነዉ።

__የመወያያ ጥያቄዎች፡-__

(1) ቅጣትን ተመጣጣኝ ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው?

(2) በቅጣት ዓላማዎችና በቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ መርሆዎች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

## 2. የቅጣት ምንነትና የቅጣት አይነቶች፣

1. በወንጀል ሕጋችን የተካተቱትን የቅጣት ዓይነቶች ማወቅ ምን ጠቀሜታ አለው ብለው ያምናሉ?
2. በቅጣት ዓላማዎችና በቅጣት ዓይነቶች መካከል ግንኙነት (መተሳሰር) ያለ ይመስልዎታል?

በተለምዶ ቅጣት ማለት አንድ ሰው ላጠፋው ጥፋት የሚወሰድበት ጉዳት የሚያስከትል እርምጃ ነው። ቅጣት በመስሪያ ቤት የዲሲፕሊን ጥፋት በመፈጸም ይወሰዳል፣ የወንጀል ድርጊት ማድረጉ በተረጋገጠው ላይም በፍርድ ቤት የሚወሰድ በአድራጊው ወይም በአጥፊው ላይ ጉዳት የሚያደርስ እርምጃ ነው።

ብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ለቅጣት የሰጠው ትርጉም "ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ በአጥፊዉ ላይ ሥርዓትን ተከትለዉ የሚጥሉበት/የሚሰነዝሩት/ የቅጣት ፍርድ ነዉ"[1] በማለት ይተረጉማል።

በወንጀል ህጋችን በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ የሚወሰዱ የተለያዩ የቅጣት አይነቶች አሉ። እነርሱም የሞት ቅጣት፣ የእስራት ቅጣት፣ መቀጮና የግዴታ ስራ ተብለው ይታወቃሉ። ከዚህ በተጨማሪ ተጨማሪ እርምጃዎችና የጥንቃቄ እርምጃዎችም አሉ።

---

[1] ብላክስ ሎዉ የህግ መዝገበ ቃለት 8ኛ እትም ገፅ 1393

## ሀ. የሞት ቅጣት

የሞት ቅጣት የሰውን ህይወት የሚያሳጣ ፍርድ ነው፡፡ የሞት ፍርድ በአጠቃላይ በተለዬ ሁኔታ ከባድ ተብለው ለሚገመቱ ወንጀሎች የሚደነገግ የቅጣት ዓይነት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 117 ላይ እንደተመለከተው የሞት ቅጣት የሚወሰነው፡-

- የተፈፀመው ወንጀል የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ወንጀሉን በሚያቋቁመው የሕጉ ልዩ ክፍል በግልፅ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ፣
- ለወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቃልልለት ምክንያት በማይኖርበት ጊዜ፣
- ወንጀለኛው ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ዕድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት ዓመት የሞላው ሲሆን ነው፡፡

ከቀድሞው የወንጀል ህግ በተቃራኒ አዲሱ የወንጀል ሕግ የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት፣ በአደባባይ በስቅላት ወይም በሌላ ኢሰብአዊ በሆኑ ዘዴዎች መፈፀም እንደሌለበት ደንግጓል(አንቀጽ 117(3))፡፡ የአፈፃፀም ዘዴው ግን ጉዳዩ በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ማረሚያ ቤት የበላይ ሕግ አስፈፃሚ አካል እንዲወሰን ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው የማረሚያ ቤቶች የበላይ ሕግ አስፈፃሚ አካል በየአካባቢው ባሉት ሁኔታዎች መሠረት አቅም በፈቀደ መጠን ሰብአዊ በሆነ መንገድ የሞት ፍርድ የሚፈፀምበትን ዘዴ እንዲወስን ለማስቻል ታስቦ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው በፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም ከፊል ኃላፊነት ላይ የሚገኝ ከሆነ የአዕምሮ ሁኔታው እስኪስተካከል ማለትም የማመዛዘን ችሎታው እስኪመለስ ድረስ፣ በፅኑ የታመመ ሰው ከሆነ ሕመሙ እስኪሻለው (እስኪፈወስ) ድረስ፣ ያረገዘች ሴት ከሆነች እስክትወልድ ድረስ አፈጻጸሙ ታግዶ ይቆያል፡፡

እንዲሁም የሞት ቅጣት ሊለወጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይኸውም ያረገዘች ሴት ህይወት ያለው ልጅ የወለደች እንደሆነና ልጁን መመገብና ማሳደግ የሚኖርባት የሆነ እንደሆነ ቀደም ሲል ተፈርዶባት የነበረው የሞት ቅጣት ወደ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ይቀየርላታል፡፡ ከዚህ በተለዬ ደግሞ የሞት ፍርድ በሚመለከተው አካል በሚሰጥ ይቅርታ

ቅጣቱ ሊለወጥ ወይም ሙሉ በሙሉ ቀሪ ሊሆን የሚችል ሲሆን እንዲሁም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ሰው በመንግስት የተሰጠ ምህረት ተጠቃሚ ከሆነ ቅጣቱ ሊቀርለትና ጥፋተኛ የተባለበትን ወንጀል ጭራሽ እንዳልፈፀመ ሊቆጠር ይችላል፡፡

## ለ. የእስራት ቅጣት

እስራት በሁለት ይከፈላል፡፡ እነርሱም ቀላል እስራት እና የማረፊያ ቤት እስራት ናቸው፡፡

## 1.1. ቀላል እስራት

ይህ ከባድነታቸው መካከለኛ ለሆኑ ወንጀሎችና ለሕብረተሰቡ አደገኛ ላልሆኑ ወንጀሎች የተደነገገ የቅጣት ዓይነት ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የቀላል እስራቱን የታች ወይም የላይ ወሰን በግልፅ የሚደነግግበት ጊዜ ያለ ሲሆን ይህ የማይሆንበት ሁኔታም አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የቀላል እስራት ቅጣቱ የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ ቀላል እስራት መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የቀላል እስራት ቅጣቱ መነሻ አስር ቀን የላይ ጣራው ደግሞ እስከ ሦስት ዓመት ይደርሳል፡፡ ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ የቀላል እስራት ጊዜ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ዓመት ቢሆንም በተለዩ ምክንያቶች የቀላል እስራት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ተመልክቷል(አንቀጽ 106(1))፡፡ እነዚህም ምክንያቶች፡-

1. ከወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ቀላል እስራት ከሶስት ዓመት ገደብ አልፎ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

2. በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ የቀላል እስራት ቅጣት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የቀላል እስራት ቅጣት ድምሩ ከአምስት ዓመት ማለፍ አይችልም፡፡ የእስራቱን ዘመን

ማርዘም እንዲቻል በማሰብም ቅጣቱን ከቀላል እስራት ወደ ፅኑ እስራት ፍርድ ቤቱ ሊቀይር አይችልም።

3. በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች በተደጋጋሚ ሲቀጣ የቀላል እስራት ቅጣት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ በተደጋጋሚ ሲቀጣ ማለት ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲሆን ማለት አይደለም።

ከቀላል እስራት ጋር በተያያዘ ሌላው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ የቀላል እስራት ቅጣት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሁሉ በቀላል እስራቱ ምትክ ፍርድ ቤቱ የግዴታ ሥራን ሊወስን እንደሚችል ተመልክቷል (አንቀጽ 107)።

## 1.2. ፅኑ እሥራት

ፅኑ እስራት ለከባድ ወንጀሎችና ለሕብረተሰቡ አደገኛ በሆኑ ወንጀለኞች ላይ የሚወሰን የቅጣት ዓይነት ነው። የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የእስራቱን ጣራ ወይም የእስራቱን የታች ወለል ወይም ሁለቱንም በግልፅ የሚደነግግበት ጊዜ ያለ ሲሆን ይህ የማይሆንበት ሁኔታም አለ። አንዳንድ ጊዜ የፅኑ እስራት ቅጣቱ የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ የፅኑ እስራት መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የፅኑ እስራት ቅጣቱ መነሻ አንድ ዓመት የላይ ጣራው ደግሞ እስከ ሀያ አምስት ዓመት ይደርሳል። ሆኖም በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል በግልፅ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ የፅኑ እስራት ዘመን እስከ ወንጀለኛው የዕድሜ ፍፃሜ ድረስ ሊቀጥል ይችላል።

በፅኑ እስራት የተቀጣ ወንጀለኛ አደገኛ ነው ተብሎ ስለሚገመት የአፈፃፀም ሁኔታ ከቀላል እስራት የአፈፃፀም ሁኔታ በይበልጥ ይከብዳል በማለት ደንግጓል (አንቀጽ 108(2))። በዚህም መሠረት በቀላል እስራት የተቀጣ ሰው በፅኑ እስራት ከተቀጣ ወንጀለኛ የተሻለ የመንቀሳቀስና ሌሎች መብቶች ባለበት ሁኔታ የተፈረደበትን እስራት እንዲፈፅም ይደረጋል ወይም ሊደረግ ይገባል።

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ቀላል እስራት የሚፈፀመው በእስር ቤቶች፣ ፅኑ እስራት የሚፈፀመው ደግሞ በወህኒ ቤቶች ስለመሆኑ ተመልክቶ የሚገኝ ሲሆን (ቁጥር 105(2) እና ቁጥር 107(2))፤ አዲሱ ሕግ ደግሞ እስረኞቹ በተለያዩ ሥፍራ መታሰር ያለባቸው መሆኑና በእስራቱ አፈጻጸም ላይ ልዩነት ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላልም ሆነ ፅኑ እስራት የተወሰነባቸው ወንጀለኞች ቅጣታቸውን የሚፈፅሙት ለዚሁ ሥራ በተሰናዱ ማረሚያ ቤቶች ስለመሆኑ ደንግጓል (አንቀጽ 106(2) እና አንቀጽ 108(2))።

በቀላልም ሆነ በፅኑ እስራት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ወንጀለኞች የመስራት ግዴታ አለባቸው። በዚህም መሠረት ሥራ የየትኛውም ዓይነት የእስራት ቅጣት አፈጻጸም አካል ነው።

## <u>ሐ. የገንዘብ ቅጣት (መቀጮ)</u>

መቀጮ ወይም የገንዘብ ቅጣት የወንጀል አድራጊውን የገንዘብ ወይም የንብረት ባለቤትነት መብት የሚነካ ቅጣት ነው። መቀጮ የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ሲሆን ገቢ የሚደረገውም ለመንግሥት ነው። የገንዘብ ቅጣት በወንጀል የደረሰ ጉዳትን የማስተካከል ዓላማ የለውም፣ መጠኑም የሚለካው ከደረሰው ጉዳት አንጻር አይደለም። የሚለካው ከተፈፀመው ወንጀል ከባድነትና ከተቀጭው የመክፈል አቅም አንጻር ነው።

መቀጮ ለብቻው ወይም ከሌሎች ቅጣቶች ጋር ሊወሰን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሕጉ መቀጮን ከቀላል እስራት ጋር በአማራጭ የሚደነገግ ሲሆን በሕጉ ልዩ ክፍል የሚገኙ አንቀጾች በግልፅ ባይደነግጉም መቀጮ የእስራት አማራጭ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊነቱን ካመነበት ሁለቱንም ዓይነት ቅጣት አጣምሮ መወሰን እንደሚችል ተደንግጓል (ቁጥር 91)። አንዳንድ ጊዜ የመቀጮው ቅጣት የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ መቀጮ መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በአዲሱ የወንጀል ህግ የመቀጮ ቅጣቱ መነሻ አስር ብር የላይ ጣራው ደግሞ አስር ሺህ ብር ነው። ተቀጪው ህጋዊ ሰውነት ያለው ሲሆን

ደግሞ የመቀጮ ቅጣቱ መነሻ አንድ መቶ ብር ጣሪያው ደግሞ አንድ መቶ ሺህ ብር ነው(ቁጥር 90)፡፡

የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የእስራትን ቅጣት አስቀምጦ መቀጮን በአማራጭ በሚደነግግበትና ተቀጪው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ እስራት ወደ መቀጮ የሚለወጥበትን ሁኔታ የሚያመለክት አዲስ ድንጋጌም አለ (ቁጥር 90(3))፡፡ በዚህ መሠረት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ አስር ሺህ ብር፣ እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃያ ሺህ ብር፣ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃምሳ ሺህ ብር፣ ከአስር ዓመት በላይ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል በሕግ የሰውነት በተሰጠው ድርጅት ላይ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ወንጀልን በሚያቋቁመው የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ መቀጮ ብቻ በተደነገገ ጊዜ እና ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው አካል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የቅጣቱን መጠን የሚወስነው ለተፈጥሮው ሰው ከተቀመጠው ቅጣት አምስት እጥፍ በማድረግ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ ቁጥር 90(4) ላይ ተደንግጓል፡፡

የተፈጥሮ ሰውን በተመለከተ ወንጀሉ የተፈፀመው በአፍቅሮ ንዋይ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ 10 ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል ተብሎ በቀድሞው ሕግ ላይ ተደንግጎ የነበረው (ቁጥር 90) በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቅጣቱ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል ተብሎ ተሻሽሏል (ቁጥር 92)፡፡

በመሠረቱ የገንዘብ ቅጣት ወዲያውኑ መከፈል ይኖርበታል፡፡ ተቀጭው ገንዘቡን ወዲያው መክፈል ባይችል አስከ ስድስት ወር የመክፈያ ጊዜ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል (ቁጥር 93(2))፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተቀጭው መቀጮውን በየጊዜው እየከፈለ እንዲጨርስ ፍርድ ቤቱ ከሶስት ዓመት ሳልበለጠ የመክፈያ ጊዜ ሊሰጠው እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ቁጥር 93(2))፡፡

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንድ ጥፋተኛ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ካልቻለ ወደ እስራት እንደሚለወጥ ይደነግግ የነበረው /ቁጥር 94/ ተሠርዟል፡፡ ለመሠረዙ በምክንያትነት የተሰጠው ድሀውን ወገን የሚጎዳ የቅጣት አፈፃፀም በመሆኑ ፍትሐዊ አይደለም የሚል ነው፡፡

በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ጥፋቱ ቀላልም ይሁን ከበድ ያለ፣ የመቀጮው መጠን አነስተኛም ይሁን ከፍ ያለ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ያቃተው ሰው ለመንግስት ወይም ለሕዝባዊ አገልግሎት ድርጅት በማገልገል ወይም የግዴታ ሥራ በመስራት ቅጣቱን እንዲፈፅም ይደረጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተቀጭው ለምን ያህል ጊዜ ሥራውን ሊሠራ እንደሚገባው መግለፅ ያለበት ሲሆን የሚወሰነው ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

## መ. የግዴታ ሥራ

የግዴታ ሥራ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሰርቶ የሚያገኘውን ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ የሚያደርግበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ጥፋተኛው የፈፀመው ወንጀል የሚያስከትለው ቅጣት ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት የሆነ እንደሆነና ጥፋተኛውም ለህብረተሰቡ አደገኛነት የሌለው መሆኑ ከታመነበት ፍርድ ቤቱ በእስራቱ ምትክ ከአንድ ቀን እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ወንጀለኛው የግዴታ ሥራ እንዲሰራ ለመወሰን ይችላል (አንቀጽ 103)፡፡ በዚህም መሠረት እስራት ወደ ግዴታ ሥራ እንዲለወጥለት አንድ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በይገባኛል የሚጠይቀው ጉዳይ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በሕግ የተቀመጠውን መመዘኛ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደ አግባብነቱ እስራቱ ወደ ግዴታ ሥራ እንዲለወጥ ወይም እስራቱ እንዲፈፀም የሚያደርግበት ነው፡፡

የግዴታ ሥራ የነገሩ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት የተቀጪውን ነጻነት ከመገደብ ጋር እንዲፈፀም ፍርድ ቤቱ ሊወስን የሚችል ሲሆን፣ በተለይም ደግሞ ተቀጪው ነጻነቱ ሳይገደብ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ቅጣት ተወስኖበት ይህን የተወሰነበትን ቅጣት በአግባቡ ሳይወጣ ከቀረ ተቀጪው ከአንድ የስራ ቦታ፣ ከአንድ አሰሪ ዘንድ፣ ከአንድ የስራ ተቋም ሳይለቅ

ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው ሳይወጣ ወይም በመንግሥት ባለሥልጣኖች ከሚጠበቅ ከአንድ የተወሰነ ሥፍራ ሳይለይ የግዴታ ሥራውን እንዲያከናውን ፍርድ ቤቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በእስራት ምትክ በግዴታ ሥራ ጥፋተኛው እንዲቀጣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ከተቀጪው ገቢ ላይ እየተቀነሰ ለመንግሥት ገቢ የሚሆነውን የገንዘብ ልክ፣ የግዴታ ሥራው የሚፈፀምበትን ሥፍራ፣ ቅጣቱ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም በተቀጪው ላይ የሚደረገውን የቁጥጥር ዓይነት ማመልከት ያለበት ሲሆን ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የሚወሰነው መጠን ከተቀጪው የድካም ዋጋ ወይም በሥራ ፍሬው ከሚያገኘው ጥቅም ከአንድ ሦስተኛ መብለጥ አይችልም፡፡

በእስራት ምትክ በግዴታ ሥራ እንዲቀጣ የተወሰነበት ወንጀለኛ በፍርድ ቤቱ የተጣለበትን ውሳኔ የጣሰ ወይም በውሳኔው መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ሳይፈፀም የቀረው የግዴታ ሥራ ወደ ቀላል እስራት ተለውጦ ቅጣቱን እንዲፈፅም ይደረጋል (አንቀጽ 104(2))፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ ከተወሰነበት የግዴታ ሥራ ዘመን ውስጥ ግማሹን በትክክል ፈፅሞ ከሆነ ይኸው ተይዞለት ላልፈፀመው የግዴታ ሥራ ዘመን ብቻ የቀላል እስራት ቅጣት ይጣልበታል ማለት ነው፡፡

## ሠ. ተጨማሪ ቅጣቶች

ህጉ ከዚህ በላይ ከተቀመጡት ቅጣቶች በተጨማሪ ተጨማሪ ቅጣቶችንም ፍርድ ቤቱ ሊጥል እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ተጨማሪ ቅጣቶች ራሳቸውን ችለው የሚጣሉ ቅጣቶች ሳይሆኑ በማሚያነት የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ተጨማሪ ቅጣቶችን ለመጣል በልዩ ክፍሉ በወንጀል ድንጋጌው ላይ ተዘርዝረው መገኘት አይኖርባቸውም፡፡ ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ፣ ጥፋተኛው ይቅርታ እንዲጠይቅ ማዘዝ በተጨማሪ ቅጣትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ወንጀሉ በጣም ቀላል በሆነ ጊዜ እነዚህ ቅጣቶች ለዋናው ቅጣት ምትክ ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉም ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ (ቁጥር 122(2))

ከዚህ በተጨማሪ ከመብት መሻር፣ ከመከላከያ ሰራዊት አባልነት ማስወገድ ወይም ከደረጃ ዝቅ ማድረግ በተጨማሪ ቅጣትነት ሊወሰኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

## ረ. የጥንቃቄ እርምጃዎች

የወንጀል ህጉ ከዚህ በተጨማሪ ወንጀለኛው የተወሰነ ቦታ እንዳይደርስ፣ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዳይወጣ ወዘተ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ፍርድ ቤት ሊወስን እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡ (ከቁጥር 129-153)

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

(1) በፅኑ እስራት ቅጣትና በቀላል እስራት መካከል ያለው አንድነትና መሠረታዊ ልዩነት ምንድን ነው?

(2) በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106 እና 108 እንደተመለከተው ቀላል እስራት የሚወሰነው ከባድነቱ መካከለኛ ለሆነ ወንጀልና ለሕብረተሰቡ እጅግ አደገኛ ባልሆነ አጥፊ ላይ ሲሆን የፅኑ እስራት ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ ለከባድ ወንጀልና ለሕብረተሰቡ በተለይ አደገኛ በሆነ ወንጀለኛ ላይ ነው፡፡ አንድ ወንጀል ከባድ ወይም መካከለኛ የሚባለው በምን መመዘኛ ነው? የአንድ ወንጀለኛ አደገኛነት የሚለካውስ በምን መንገድ ነው? ከከባድነት አንጻር የስርቆት ወንጀል እንዴት ነው የሚታየው?

(3) የፅኑ እስራት በተደነገገበት ወንጀል ጥፋተኛ ለሆነ ሰው እጅግ ብዛት ያላቸው የቅጣት ማካበጃ ምክንያቶች ቢቀርቡበት ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲሆን ፍርድ ቤት መወሰን ይችላል?

(4) በመ.ቁ. 60143 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 (3) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ አንድ ሰው በመግደል እና የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 279/1956 አንቀጽ 5(4) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ "...ተከሳሽ እስካሁን የታሰረው የእስራት ቅጣቱ አካል ሆኖ ይታሰብለት" በማለት ፍርድ ቤቱ በ ሦስት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 5000.00 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ተቀጪው ታስሮ የቆየበት ጊዜ መቆጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን ያህል ዓመት ቀላል እስራት ተወስኖበታል ወይም ፅኑ እስራት ተወስኖበታል በማለት (ምን ያህሉ እንደሚያዝለት ለማረሚያ ቤት ውሳኔ በመተው) በፍ/ቤት የሚወሰን ቅጣት ከሕግ አንጻር ያለው አግባብነት እንዴት ይታያል?

(5) የወንጀል ሕጉ በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ ሰዎች ላይ እንደ ሁኔታው ለመንግስት ወይም ለሕዝባዊ አገልግሎት ድርጅት በመስራት ወይም የግዴታ ሥራ በመስራት ቅጣታቸውን እንዲፈፅሙ መወሰን እንዲችሉ ለፍርድ ቤቶች ሥልጣን ቢሰጥም በዚህ

መሠረት ውሳኔዎች ሲሰጡ ብዙም አይስተዋልም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል? ይህ ሁኔታ ያስከተለው ጉዳት ይኖር እንደሆን ተወያዩበት፡፡

(6) በአጠቃላይ በቅጣት ዓይነቶችና በቅጣት ዓላማዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመርምሩ፡፡

(7) ከዋና ከዋና ቅጣቶች በተጨማሪ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሌሎች ተደራቢ ቅጣቶች በአንድ ወንጀለኛ ላይ ሊወሰኑበት ይችላሉ፡፡ ማለትም ለተፈፀመው ወንጀል አግባብነት ያለው ድንጋጌ ላይ ባይመለከትም ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ ተጨማሪ ቅጣቶችን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ (ሀ) እነዚህ የተጨማሪ ቅጣት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? (ለ) ተጨማሪ ቅጣቶች የሚወሰኑበት ዓላማ ምንድን ነው? (ተወያዩበት)

## 3. ስለቅጣት አወሳሰን የወንጀል ህጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣

የወንጀል ህጋችን ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የቅጣት መነሻና መድረሻ አስቀምጧል፡፡ ይሁንና እነዚህን የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ስለሆነ፣ ዳኛው ለቅጣት አወሳሰኑ እንዲረዳው በመጀመሪያው ታላቅ ክፍል አንደኛው መጽሀፍ ርእስ ሶስት ስለቅጣት አወሳሰን የሚረዱ ድንጋጌዎችን እናገኛለን፡፡ በዚህ ክፍል እነዚህን አጠቃላይ ድንጋጌዎች ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

ቅጣት ሲወሰን ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በወንጀል ህጉ በቁጥር 88(2) የተመለከቱ ሲሆን፣ እነርሱም፣

- የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣
- ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣
- ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሀሳቡን አላማ፣
- የግል ኑሮውን ሁኔታ፣
- የትምህርቱን ደረጃ፣
- የወንጀሉ ከባድነት እና
- የአፈጻጸሙ ሁኔታዎች

የሚሉ ናቸው፡፡

የገንዘብ መቀጮ ሲወሰንም ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸውን ነጥቦች በቁጥር 90(2) ተመልክቶ እናገኛለን፡፡

- የወንጀሉን ክብደት
- የአደገኛነቱን መጠን፣
- የሀብቱን ሁኔታ፣
- የገቢ ምንጩን፣
- ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ያለበትን ሸክም፣
- የሙያ ስራውን፣
- ከስራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን
- እድሜውን፣
- የጤንነቱን ሁኔታ

የሚሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል የሚያስችሉ ምክንያቶችንም በሚመለከት በዚሁ ክፍል ተዘርዝረው እናገኛለን፡፡ እነዚህም ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች እንዲሁም ልዩ የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች ተብለው ተዘርዝረዋል፡፡

## 3.1. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች፣

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በቁጥር 84 የተመለከቱ ሲሆን እነርሱም፣

ሀ. ወንጀሉን ያደረገው በከሀዲነት ወይም በወስላታነት፣ወራዳነትን ወይም መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ጥላቻ፣ስግብግብነት፣መጥፎ ነገርን ለመስራት ወይም ሰውን ለመጉዳት ፍጹም ፈቃደኛ በመሆን፣በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት እንደሆነ፣

ለ. ስልጣኑን፣ ተግባሩን ወይም የተጣለበትን እምነት ወይም ሀላፊነት ያላግባብ በመገልገል እንደሆነ፣

ሐ. ወንጀለኛው በቀድሞ ጥፋተኝነቱ፣ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጎ መያዙ፣ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜ ቦታና የአፈጻጸሙ አኳኋን በተለይም

በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሳሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሳሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ፣

መ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ወንጀል ለመፈጸም በተደረገ ስምምነት መሰረት ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ወንጀል ለመፈጸም ከተቋቋመ ቡድን ጋር በመስማማት ወይም አባል በመሆን ይልቁንም እንደወንጀል ቡድን ሹም፣ አደራጅ ወይም መሪ በመሆን እንደሆነ፣ ወይም

ሠ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በእድሜው፣ በጤንነቱ፣ በኑሮው ወይም በስራው ሁኔታ ልዩ ጥበቃ በሚያሻው ሰው ላይ በተለይም ለመከላከል አቅም በሌለው፣ መንፈሰ ደካማ፣ በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ፣ እስረኛ ወይም በቅርብ ዘመዱ ላይ ወይም የበላዩ ወይም የበታቹ በሆነ ሰው ላይ፣ በህግ በተቋቋመ ባለስልጣን ወይም የስራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የህዝብ አገልጋይ በሆነ ሰራተኛ ላይ የሆነ እንደሆነ፣

የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ከሞላ ጎደል በቁጥር 88 በጥቅሉ ከተቀመጡት መለኪያዎች ከፊሉን በዝርዝር ያስቀመጡ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

__የመወያያ ጥያቄዎች__፤

(1) የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ አንድ ፍ/ቤት የሚወስነው ቅጣት ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን የቅጣቱን ዝቅተኛ፣ ከፍተኛ ወይስ የዝቅተኛውንና የከፍተኛውን ቅጣት አማካይ ሊሆን ይገባል?

(2) በመ.ቁ. 44617 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(2) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ፣ 3ኛ ተከሣሽ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 407(1) (ሀ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ናቸው ከተባለ በኋላ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ "...በግራ ቀኙ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ምክንያት የለም፡፡... የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በስምንት ወራት ቀላል እስራት፣ 3ኛ ተከሣሽ በሶስት ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ" በማለት ፍርድ ቤቱ ወስኗል፡፡ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ አግባብነት ይመርምሩ፡፡

(3) ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ከ "ልዩ" የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች የሚለያቸው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?

(4) “አንድ ሰው በፈፀመው አንድ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ ቅጣቱ በሚወሰንብት ወቅት ብዛት ያላቸው እና ክብደታቸው ከፍተኛ የሆነ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቢኖሩ በአጥፊው ላይ የሚወሰነው ቅጣት ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ ከተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ጣራ ሊያልፍ አይችልም”፡፡ ይህ አቀራረብ ትክክል ነው ብለው ያስባሉ? ለምን? ተወያዩበት፡፡

(5) በመ.ቁ. 38528 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ በ1974 ዓ.ም በወጣው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 23(1)(ለ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ በፈፀመው በሥልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በፍርድ ቤቱ ከተባለ በኋላ ዐቃቤ ሕግ በሚከተለው መልኩ የቅጣት አስተያየት አቅርቧል፡- “በተከሣሹ ላይ ከተጠቀሰበትና ከቀረበበት ክስ በ1ኛው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቷል፤ በዚህ መሠረት በወ/ሕ/ቁ. 84(1) (ለ) እና (መ) መሠረት ተከሣሹ ወንጀሉን ያደረገው ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆኑ በዚህ መሠረት በተከሣሹ ላይ ቅጣት ከብዶ እንዲወሰን እንጠይቃለን” በማለት አመልክቷል፡፡ የዐቃቤ ሕግን የቅጣት አስተያየት በወንጀል ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ይመርምሩ፡፡

(6) በመ.ቁ. 07537 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ስድስት ተከሣሾች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ በኋላ ዐቃቤ ሕግ የቅጣት አስተያየት ሲያቀርብ “… 5ኛ እና 6ኛ ተከሣሾች ወደ ፍርድ አደባባይ ቀርበው መከራከር ሲገባቸው መሰወራቸው ቅጣቱን እንዲያከብድ የሚያደርግ በመሆኑ…” ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰንለት ሲጠይቅ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ደግሞ “… ጉዳያቸው በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው ተከሣሾች መሰወራቸው አደገኛነታቸውን የሚያሳይ ነው” በማለት በቅጣት ማክበጃ ምክንያትነት ወስዶታል፡፡ የዐቃቤ ሕግን የቅጣት አስተያየት እና የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በወንጀል ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ይመርምሩ፡፡

## 3.2. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች በቁጥር 82 የተመለከቱት ሲሆኑ፣ እነርሱም፣

ሀ. ወንጀለኛው ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም እንደሆነና ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ፣

ለ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በተከበረና በግል ጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ፍላጎት ወይም ከፍ ባለ ሀይማኖታዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማህበራዊ እምነት ተነሳስቶ እንደሆነ፣

ሐ. ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው ከፍተኛ ቁሳዊ እጦት ወይም የህሊና ስቃይ ደርሶበት፣ ከፍ ያለ አደጋ የሚያመጣ ነገር የተቃጣበት መስሎት፣ መሰረት ያለው ፍርሀት አድሮበት ወይም ደግሞ ሊታዘዝለት በሚገባው ወይም በስልጣኑ ስር በሚያስተዳድረው ሰው ተጽእኖ ምክንያት እንደሆነ፣

መ. ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ሰው ጠባይ ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት፣ በከባድ ጸብ ቀስቃሽነት ወይም በአስጸያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፣ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ፣ ወይም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው ስሜትን በሚለውጥ ሁኔታ ወይም ምክንያት ባለው የመንፈስ ሁከት ላይ ሆኖ እንደሆነ ወይም፣

ሠ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረገ በኋላ በእውነት የተጸጸተ መሆኑን፣ በተለይም በደል ላደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ፣ ወይም ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትህ አካላት በማቅረብ ወይም የወንጀሉ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን በመካስ መጸጸቱን በተግባር አሳይቶ እንደሆነ ወይም ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ ነው።

የሚሉ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ከፊሎቹ በቁጥር 88(2) ውስጥ ያሉትን መልሰው የሚጠቅሱ ናቸው።

ከዚህ በላይ በህጉ ከተመለከቱት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ሌላ በቂ የሆነ ምክንያት ዳኛው ካገኘ በዚህ መሰረትም ቅጣቱን ማክበድ ወይም ማቅለል እንደሚችል በቁጥር 86 ተደንግጓል። ይሁንና ዳኛው እነዚህን ምክንያቶች ሲቀበል ለምን እንደተቀበለ መግለጽ እንደሚኖርበት ተመልክቷል።

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ የሚከብድበትን መጠን ወይም የሚቀልበትን ደረጃ በሚመለከት በወንጀል ህጉ ከቁጥር 179-183 ተዘርዝረው እናገኛለን፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>፤

(1) ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ከ "ልዩ" የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚለያቸው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?

(2) ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እና ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያች አንድ ላይ በሚገኙበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ የሚከናወነው እንዴት ነው?

(3) "አንድ ሰው በፈፀመው አንድ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ ቅጣቱ በሚወሰንብት ወቅት ብዛት ያላቸው እና ክብደታቸው ከፍተኛ የሆነ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ቢኖሩ በአጥፊው ላይ የሚወሰነው ቅጣት ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ ለተደነገገው የቅጣት ዓይነት በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ዝቅተኛ የቅጣት ወለል ሊወርድ አይችልም"፡፡ ይህ አቀራረብ ትክክል ነው ብለው ያስባሉ? ለምን? ተወያዩበት፡፡

(4) በመ.ቁ. 54827 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በፈፀመው ወንጀል ጥፋተኛ ነው ከተባለ በኋላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የቅጣት ውሳኔ "... ሟችን ከአደጋው በኋላ ወደ ህክምና ተቋም ማድረሱ፣ ለህግ አካል እጁን መስጠቱ የቅጣት ማቅለያ ሊሆኑት እንደሚገባ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82(1)(ሀ) ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ፤ እንዲሁም አባትና ወንድሙን ጨምሮ የቤተሰብ አስተዳደሪ መሆኑም የቅጣት ማቅለያ ሊሆኑት እንደሚችሉ ፍርድ ቤቱ ወስዷል፤ የወንጀሉ አፈጻጸምም በድንገት የተፈፀመ መሆኑንም ሆነ ካሳ ለመክፈል ሞክሬ ነበር የተባለውንም ለቅጣቱ ማቅለያነት ግምት ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል፡፡" በማለት ተከሣሹ በአንድ ዓመት ቀላል እስራትና ሦስት ሺህ ብር እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በወንጀል ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ይመርምሩ፡፡

## 3.3. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች

ህጉ ከዚህ በላይ ከተገለጹት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በተጨማሪ ልዩ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ዘርዝሮ እናገኛለን፡፡

*ደጋጋሚ ወንጀለኛነት* -

አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ለማለት በወንጀል ህጉ ሊሟሉ የሚገባቸው መመዘኛዎችን እናገኛለን፡፡

1. ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 67 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት የመጀመሪያው መመዘኛ በወንጀለኛው ላይ ከዚህ ቀደም የወንጀል ክስ ቀርቦበት የእስራት ቅጣት የተወሰነበት መሆን አለበት፡፡ አዲሱን ወንጀል በፈፀመበት ወቅት ቀደም ሲል ፈፅሞት በነበረው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የወንጀል ክስ ያልቀረበበት ወይም ክስ ቢቀርብበትም ገና በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔና ቅጣት ያልተጣለበት ከሆነ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መስፈርት አልተሟላም ማለት ነው፡፡
2. ከዚሁ ጎን ለጎን ሊረሳ የማይገባው ነጥብ በመጀመሪያው ወንጀል ቅጣቱ የእስራት ሊሆን የሚገባው መሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ሰው በመጀመሪያው ወንጀል የተፈረደበት የገንዘብ መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም ወቀሳና ማስጠንቀቂያ ከሆነ ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ አይሆንም ማለት ነው፡፡
3. አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት በሶስተኛነት ሊታይ የሚገባው መመዘኛ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም የተወሰነበትን ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት፤ ወይም በምህረት ወይም በአዋጅ ምህረት ቅጣቱ ከቀረለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆን አለበት፡፡
4. አራተኛው የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መመዘኛ ወንጀለኛው አዲሱን ወንጀል የፈፀመው አስቦ/intentionally/ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቸልተኝነት የተፈፀመ ወንጀል ደጋጋሚ ወንጀለኛ አያሰኝም ማለት ነው፡፡

5. አምስተኛው መመዘኛ ወንጀለኛው የፈፀመው አዲስ ወንጀል ቢያንስ እስከ ስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሊሆን ይገባል፡፡

በወንጀለኛው የተፈፀመው አዲስ ወንጀል ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት በህጉ ላይ በተደነገጉት የደጋጋሚነት መስፈርቶች መሰረት ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው የሚያሰኘው ከሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 188(1) ላይ እንደተደነገገው በመርህ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የቅጣት ጣራ እጥፍ እስኪሆን ድረስ ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል፡፡ በመሆኑም ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበትን የሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ የቅጣት ጣራ አልፎ ወንጀለኛው ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ከተመለከተው የቅጣት ጣራ እጥፍ እስኪሆን ድረስ ፍርድ ቤቱ መወሰን ይችላል ማለት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በወንጀል ሕጉ የተካተተው ለደጋጋሚ ወንጀለኛ በመርህ ደረጃ የሚኖረው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ነው፡፡ የተደጋገሙት ወንጀሎች ቁጥር ብዛት ያላቸው ከሆነ እንዲሁም የወንጀለኛው የአጥፊነት ደረጃና የድርጊቱ አደገኛነት ከባድ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ላይ የተጠቀሰውን የቅጣት ጣራ በማለፍ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት እስከሰፈረው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ሊወስን ይችላል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 188(2))፡፡ እንዲሁም ወንጀለኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ለመጨረሻው አዲስ ወንጀል የሚጥለው ቅጣት በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ላይ ከተጠቀሰውን ቅጣት ጣራ የግድ በማለፍ መሆን ያለበት ስለመሆኑ በፍርድ ቤቱ ላይ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ ተደንግጓል፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች፤***

(1) በደጋጋሚ ወንጀለኛነት በተደጋጋሚ መቀጣት ወይም ሪኮርድ ያለው በመሆን መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

(2) በደጋጋሚ ወንጀለኛ ላይ በተለዬ ሁኔታ ቅጣት እንዲከብድበት የሚደረገው ለምንድን ነው?

(3) አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ ከተመለከተው ቅጣት ጣራ በላይ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ከወንጀል ሕግ መርህ አንጻር እንዴት ይታያል? (አይጣረዝም ይላሉ)፡፡

## ተደራራቢ ወንጀሎች

ተደራራቢ ወንጀሎች (concurrence offences) በአጠቃላይ በአንድ ሰው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ሁለት ወይም ቁጥራቸው ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተደራራቢ ናቸው ሊባሉ የሚችሉት ሁለተኛው ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት መጀመሪያ በተፈፀመው ወንጀል ላይ ፍርድ አልተሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

አንድ ሰው ተመሳሳይ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም እንደ አንድ ወንጀል የማይቆጠሩ ወንጀሎችን ሲፈፅም ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ ማለትም የተለያዩ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም በተለያዩ የወንጀል ድንጋጌዎች ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን በመፈፀም ወይም በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም ደግሞ በአንድ ድርጊት የጣሰው አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ካደረሰ ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈፀመ ይቆጠራል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 60)፡፡

ለተደራራቢ ወንጀሎች የሚኖረውን የቅጣት አወሳሰን ስንመለከት፡-

(1) ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ከተወሠነ ይህ ውሳኔ ለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሠነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል (አንቀጽ 184(1)(ሀ))፡፡ ይህም ማለት ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንዱ ምክንያት የሞት ቅጣት ወይም የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት፣ የ25 ዓመት ፅኑ እስራት ወይም የአምስት ዓመት ቀላል እስራት ከተወሠነ በሌሎች ተመሣሣይ ዓይነት ቅጣት በሚያስፈርዱ ወንጀሎች ምክንያት ከተገለፀው ቅጣት በላይ መወሠን አይቻልም፡፡ (በአንቀጽ 184/1//ሀ/ የተደነገገው ሁኔታ ቅጣቱ ቢከብድም ከተደራረቡት ወንጀሎች በአንደኛው ውስጥ በሕጉ ልዩ ክፍል ቅጣቱ ተካትቶ /ተሸፍኖ/ የምናገኝበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው)፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ከባድ ለሆነው ለአንደኛው ወንጀል የሞት ቅጣት፤ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል

የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መወሰኑን ትቶ ዝቅ ያለ ቅጣት ከወሠነ፤ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አክብዶ መወሠን ይችላል፡፡

(2) ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ የየትኛውም ወንጀል ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል ካልሆነና ወንጀሎቹ በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ከሆኑ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንዲደመር ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምንጊዜም ቢሆን ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ማለፍ አይቻልም/አንቀጽ 184/1//ለ/፡፡

(3) አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በገንዘብ ቅጣት (በመቀጮ) የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች የሆኑ እንደሆነ ወይም ከሌሎች ቅጣት ጋር ተጣምረው ለተደራራቢ ወንጀሎቹ የገንዘብ ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ የሚጣሉ በሚሆንበት ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው የገንዘብ ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል፡፡ ሆኖም ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈፀመ ካልሆነ በቀር ምንጊዜም ቢሆን በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው የመቀጮ ቅጣት አጠቃላይ ድምር በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ወሠን ማለፍ አይችልም፡፡

የመውረስና የገንዘብ መቀጮ በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን በተመለከተ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተተው ሀሳብ ተመሳሳይ ነው፡፡ ከተደራራቢዎቹ ወንጀሎች በአንዱ ምክንያት የተቀጪው ንብረት እንዲወረስ ከተወሰነ በሌላው ወንጀል ምክንያት መቀጮ በተጨማሪ ሊወሠን አይችልም /ቁጥር 189(ሠ)፣ አንቀጽ 184(1)(ሠ)/

በአንድ ድርጊት አንድ ሰው ተደራረቢ ጣምራ ወንጀሎች የፈፀመ እንደሆነ ደግሞ፡-

- ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው ከዚህ በታች ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭ ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን አክብዶ ይወስናል (አንቀጽ 187(1))።
- ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕጉን ጥሶ ከሆነ ወይም ግልፅ የሆነ መጥፎ ፀባይ አሳይቶ እንደሆነ ግን በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል።

ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች ተፈፅመው በተገኙ ጊዜ ግን ጥፋተኛው ከተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንደኛውን አስቦ ያደረገ እንደሆነ በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ሀ)፣ ጥፋተኛው ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ለ)፣

<u>***የመወያያ ጥያቄዎች፤***</u>

(1) አንድ ሰው በአንድ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀጣ በኋላ ሌላ ወንጀል ሲፈጽም እና ሁለት ወንጀሎችን በተከታታይነት ሲፈጽም ያለው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ልዩነት ምንድን ነው? ለልዩነቱ ምክንያቱ ምንድን ነው?

(2) አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰላ ተወያዩበት።

(3) አንድ ሰው ቁጥራቸው ሀያ የሚሆኑ በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎችን ቢፈፅምና ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት ምን ያህል ነው? ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን በፅኑ እስራት (የእድሜ ልክ እስራትን ሳይጨምር) የሚያስቀጡ ወንጀሎችን ቢፈፅምስ ሊጣልበት የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት ምን ያህል ይሆናል? (ገደብ አለ የሚሉ ከሆነ መኖሩ ለምን አስፈለገ? የወንጀል ሕጉን ዓላማስ ያሳካል ብለው ያምናሉ?)

## <u>3.4. ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

በአዲሱ የወንጀል ሕግ በልዩ ሁኔታ ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችሉ ሁኔታዎች በቁጥር 83 ላይ በግልፅ የተጠቀሱት ምክንያቶች ዝምድናና የጠበቀ ወዳጅነት ቢሆኑም በሕጉ ጠቅላላ ወይም ልዩ ክፍል ውስጥ ፍርድ ቤቱ በመሠለው ቅጣት ማቅለል ይችላል የተባለባቸው ምክንያቶች ሁሉ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ናቸው (ቁጥር 83(1))፡፡

ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ያለውን የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 83(2) እና 122 ላይ እንደተመለከተው የወንጀለኛው ጥፋት በጣም ከባድ ካልሆነና የዝምድና ወይም የወዳጅነት ትስስሩ /ግንኙነቱ/ እጅግ ጥብቅ ከሆነ ወንጀለኛውን በማስጠንቀቅ ወይም በወቀሳ ብቻ ፍርድ ቤቱ ሊያልፈው ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ ባሉ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን ፍርድ ቤቱ በመሠለው ቅጣትን ማቅለል የሚችል ቢሆንም የሚወሰነው ቅጣት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ ዓይነት ከተደነገገው መነሻ ቅጣት ዝቅ ሊል አይችልም /አንቀጽ 180/፡፡ ይህም ማለት፡-

- የገንዘብ ቅጣት በአንቀጽ 90 መሠረት ከብር አስር ሊያንስ አይችልም፡፡
- የቀላል እስራት ቅጣት በአንቀጽ 106 መሠረት ከአስር ቀን ሊያንስ አይችልም፤
- የፅኑ እስራት ቅጣት በአንቀጽ 108 መሠረት ከአንድ ዓመት ሊያንስ አይችልም፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>፤

(1) የወንጀል ሕጉ ዝምድና ለአንዳንድ ዓይነት ወንጀሎች እንደ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተደርጎ እንደሚወሰድ የደነገገ ቢሆንም የዝምድናውን ደረጃ በግልፅ አላመለከተም፡፡ ዝምድና አለ ወይም የለም የሚለውን ለመወሰን የሚቻለው እንዴት ነው?(በተለይም አገራችን በምትከተለው የፌዴራል ሥርዓት ምክንያት እያንዳንዱ ክልል በመርህ ደረጃ የራሱን መመዘኛ በመከተል በራሱ የቤተሰብ ሕግ ውስጥ ስለዝምድና ሊደነግግ የሚችል መሆኑ እዚህ ላይ ልብ ሊባል ይገባል)፤ "የጠበቀ ወዳጅነት" አለ የሚባለውስ በምን መመዘኛ ነው?

(2) በአንቀጽ 83 ላይ በግልፅ ከተመለከቱት ውጭ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ሊወሰዱ የሚችሉ ቢያንስ አምስት ጉዳዮችን (ምክንያቶችን) በመለየት በምን ደረጃ ቅጣትን እንደሚያቀሉ ተወያዩባቸው፡፡

(3) ልዩ የቅጣት ማቅለያ እና ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አንድ ላይ በሚገኙበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ የሚከናወነው እንዴት ነው?

## 4. በጥፋተኛው ላይ ለጊዜው ጥፋት አለመጣልና በገደብ ስለመልቀቅ፣

### 4.1. ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ ቅጣት አለመጣል (ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት)

የወንጀል ህጉ ወንጀል አድራጊው ጥፋተኛ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሁሉ ቅጣት እንዲጣልበት ማድረግ ዋናው አቅጣጫ ቢሆንም በተወሰኑ ሁኔታዎች ዳኛው ቅጣት ከመጣል ወይም ቅጣቱን እንዲፈጽም ከማድረግ መወሰን የሚያስችል ስልጣን እንዳለው በህጉ ተመልክቷል፡፡

በአንድ ተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛውን ሲመዝን በወንጀለኛው ላይ ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ የተቀመጠውን ቅጣት መወሰኑ ከትርፉ ይልቅ ኪሳራው ያመዝናል ብሎ በሚያምንበት ወቅት የቅጣት ውሳኔውን ከመወሰን ተቆጥቦ ለወንጀለኛው የፈተና ጊዜ ሊሰጠውና የፈተና ጊዜውን በተገቢው ሁኔታ ከተወጣ የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሊሰርዝለት ይችላል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 191 ላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ እንዲህ ዓይነት የፈተና ጊዜ በመስጠት ወንጀለኛው ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ቅጣት ሳይጥል የሚተወው ወንጀለኛው ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንዲችል እምነት ሊጣልበት የሚገባው መሆኑንና "ጥፋተኛ ነህ" መባሉ ብቻ ማስጠንቀቂያ ሆኖት እስከመጨረሻው ጠባዩን ለማሻሻል የሚያስችለው መሆኑን የገመተ እንደሆነ ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ላይ ወንጀለኛው ሊታረም ይችላል ተብሎ የሚገመትባቸው ሁኔታዎች የተዘረዘሩ ሲሆን በዚህም መሰረት ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጀል የፈፀመ፣ ጠባዩም አደገኛነት የሌለው ስለመሆኑ የሚታመንበት ዓይነት እንደሆነና አሁን ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት ወንጀል በመቀጮ፣ በግዴታ ሥራ ወይም ከሦስት ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱን ካረጋገጠ በኂላ የፈተና ጊዜ በመስጠት የቅጣት ውሳኔውን ከመወሰን ገድቦ ማቆየት ይችላል፡፡

ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠው የፈተና ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊያንስና ከአምስት ዓመት ሊበልጥ የማይችል ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤቱ በወሰነው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋተኛው ሊከተለው የሚገባውን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን በተመለከተ በውሳኔው ላይ የሚያሰፍር ሲሆን እነዚህ ደንቦች በአንድ የጥበብ መስክ ሙያ መማርን፣ በተወሰነ ሥፍራ መቀመጥን፣ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር አለመገናኘትን፣ አልኮል ከመጠጣት መቆጠብን፣ወ.ዘ.ተ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ እንዚህን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን ጥፋተኛው ተከትሎ እየፈፀመ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ወይም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለሚመለከተው የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኮሚሽን ሪፖርት የሚያቀርብ አሳዳሪ፣ ሞግዚት፣ የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኃላፊን ወይም የጠባቂነት ሥልጣን የተሰጠው አካል የጥበቃ ባልደረባን ያዝዛል፡፡

ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው በወሰነው የፈተና ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥፋት ካልፈፀመ ማለትም ጥፋተኛው የፈተና ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፈና ፈተናው መልካም ፍሬ ካስገኘ የጥፋተኝነት ውሳኔው እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

## 4.2. ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ

ፍርድ ቤት አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጠና የሚገባውን ቅጣት ከወሰነ በኋላ ወንጀለኛው ለወደፊቱ ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚገባውና ይህ ዕኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ እስከመጨረሻው ጠባዩን እንዲያሻሽል እንደሚያደርገው የገመተ እንደሆነ የቅጣቱን አፈጻጸም አግዶ የፈተና ጊዜ ለወንጀለኛው ሊሰጠው ይችላል (አንቀጽ 192)፡፡ ፍርድ ቤቱ ቅጣት እንዳይፈጸም የሚሰጠው ትእዛዝ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊመለከት የማይችል ሲሆን ከዋና ቅጣቶች በተጓደኝ የሚጣሉ ተጨማሪ ቅጣቶችን በተመለከተ ግን እንደአግባብነቱ አብረው ታግደው እንዲቆዩ ወይም ተፈጻሚ መሆናቸው እንዲቀጥል ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

በአንድ ወንጀለኛ ላይ የተወሰነ ቅጣት ሊገድብ የማይችልባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 (1) ላይ የተመለከቱ ሲሆን እነርሱም፡-

(1) ከዚህ በፊት የፅኑ እስራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እስራት ቅጣት ተወስኖበት የነበረ ከሆነና አሁን እንደገና በፈፀመው አዲስ ወንጀል ምክንያት ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት የሆነ እንደሆነ የተወሰነበት ቅጣት ሊገደብለት አይችልም፡፡

(2) ምንም እንኳ ወንጀለኛው ከአሁን በፊት ወንጀል ፈጽሞ ያልተቀጣ ቢሆንም አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ ፅኑ እስራት ቅጣት የሚፈረድበት ከሆነ ቅጣቱ ሊታገድለት አይችልም፡፡ ይህ መስፈርት በወንጀል ሕጉ እንዲካተት የተደረገ አዲስ መስፈርት ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከምን በላይ ቢፈረድበት ቅጣቱ ሊገደብለት እንደማይችል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የተደነገገ ነገር አልነበረም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሳይደነገግ በመቅረቱ ፍርድ ቤቶች ከፈለጉ እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊገድቡ ቢችሉ የሚያግዳቸው ነገር አልነበረም፡፡

ፍርድ ቤቱ ለወንጀለኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ፣ በፈተና ጊዜው ወቅት ወንጀለኛው ሊከተለው የሚገባውን የመልካም ጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን በተመለከተ ከዚህ በላይ በወንጀል ጥፋተኝነት ከተወሰነ በኋላ ቅጣት ሳይጣል ስለሚሰጥ ገደብ በቀረበው ላይ የተገለፁት ጉዳዮች ቅጣት እንዳይፈጸም ፍርድ ቤቱ በሚያግድበት ጊዜም ተፈጻሚነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው በሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥፋት ካልፈፀመ ማለትም ጥፋተኛው የፈተና ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፈና ፈተናው መልካም ፍሬ ካስገኘ በጥፋተኛው ላይ ተወስኖበት የነበረው ቅጣት እስከ መጨረሻው ቀሪ ይሆንለታል፡፡

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች፤**</u>

1. በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ ቅጣት ለመጣል/ላለመጣል (ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ ለመስጠት) መሟላት ካለባቸው መስፈርቶች ውስጥ ለዳኞች የተተው ፍቅድ ሥልጣኖች (discretions) እና ለዳኞች ያልተተውት ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ ተወያዩባቸው፡፡
2. የወንጀል ሕጉ ዳኞች በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ ቅጣት ሳይጥሉ የፈተና ጊዜ መስጠት እንዲችሉ የሚፈቅድ ቢሆንም በዚህ መሠረት ሲፈፀም ብዙም አይስተዋልም፡፡ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?
3. ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ ቅጣት ሳይጣል የፈተና ጊዜ ተሰጥቶት ፈተናው መልካም ፍሬ ካስገኘ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው?

4. በዚህ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋተኛው አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ቅጣቱ የሚወሰነው እንዴት ነው? ቀደም ሲል ታግዶለት የነበረው የቅጣት ውሳኔ ምን ይደረጋል? ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ወይስ ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው ቅጣቱ የሚጣልበት? ተወያዩበት፡፡
5. የቅጣት ውሳኔን በማገድና የቅጣት አፈጻፀምን በማገድ መካከል ያሉት መሠረታዊ ልዩነቶች ምንድን ናቸው?
6. ቅጣት እንዳይፈፀም ለማገድ/ላለማገድ መሟላት ካለባቸው መስፈርቶች ውስጥ ለዳኞች የተተው ፍቅድ ሥልጣኖች (discretions) እና ለዳኞች ያልተተውት ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ ተወያዩባቸው፡፡
7. ቅጣት ሳይፈፀምበት የታገደለት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው የተሰጠውን የፈተና ጊዜ በመልካም ሁኔታ ካሳለፈ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው?
8. በዚህ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋተኛው አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ቅጣቱ የሚወሰነው እንዴት ነው? ቀደም ሲል አፈጻፀሙ ታግዶለት የነበረው የቅጣት ውሳኔ ምን ይደረጋል? ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ወይስ ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው ቅጣቱ የሚጣልበት? ተወያዩበት፡፡
9. በወ.መ.ቁ. 51889 ቀጥሎ የተሰጠውን የእግድ ትእዛዝ  የወንጀል ሕጉ ካስቀመጣቸው መስፈርቶች አንጻር መርምሩ፡፡

ተከሣሹ የወንጀል ሕግ ቁጥር 543 (2)ን በመተላለፍ ሁለት ሰዎችን በመግደሉ እንዲሁም የወንጀል ሕግ ቁጥር 559 (2)ን በመተላለፍ በሁለት ሰዎች የአካል ጉዳት በማድረስ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ እና ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን አስተያየት ካዳመጠ በኂላ "...በወንጀል ሕግ ቁጥር 179(መ) መሠረት ተከሣሹ ጥፋተኛ ከተባለበት አንቀጽ የቅጣት መነሻ በመውረድ በሁለት ዓመት እስራትና በብር 10000.00 (አስር ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 149(5) መሠረት ፈርደናል፡፡ የእስራት ቅጣት ፍርዱን አፈጻፀም በተመለከተ ግን ተከሣሽ የሃኪም ክትትልና ህክምና የሚያስፈልገው የደም ብዛት በሽተኛ መሆኑን በሀኪም ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ የጤና ችግር እያለበት በማረሚያ ቤት ይቆይ ቢባል ሊደርስበት የሚችለውን ችግር መባባስ እንዲሁም የውጭ ዜጎችን በማስተባበር ጭምር ቤተሰብ አልባ የሆኑ ህጻናትን የሚረዱ መሆኑም ሲታይ ቅጣቱ ... ሳይፈፀም ታግዶ ለ 2 ዓመት ቢቆይ ተገቢ መሆኑን ፍርድ ቤቱ

አምኖበታል፡፡… ተከሣሽ የእስራት ቅጣቱ የተገደበለት በመሆኑ የገንዘብ ቅጣቱን እንደከፈል ከእስር እንዲፈታ …" በማለት ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

## 5. የቅጣት አወሳሰን ላይ የሚታዩ ችግሮች፣

አጠቃላይ የህጉን አቀራረጽ ስንመለከት ዳኛው ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ከማስተካከሉ በፊት በወንጀል ድንጋጌው ተፈጸመ ለተባለው ወንጀል መነሻ ቅጣት ሊወስን እንደሚገባው የሚያመለክት ነው፡፡ በመቀጠልም ዳኛው በመጀመሪያ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ማስላት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡[2] ከዚያም ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን እንደሚያቀል ይደነግጋል፡፡

ደጋጋሚ ወንጀለኛ ወይም ተደራራቢ ወንጀል ሲሆን ደግሞ መጀመሪያ በደጋጋሚነት ወይም ተደራራቢ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት ከተወሰነ በኋላ በቀጣይነት ጠቅላላ ማክበጃዎችን እንዲሁም ማቅለያዎችን መሰረት አድርጎ በቅደም ተከተል ቅጣቱ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

ይሁንና ማክበጃውን ተግባራዊ ለማድረግ፣ መነሻ ቅጣቱ ስንት ነው? ለምሳሌ በ407(1) መሰረት መነሻው 1 አመት ሲሆን መድረሻው 10 አመት ነው፡፡ ይሁንና ዳኛው ከየት ነው መነሳት ያለበት? ከአንድ አመት? ከአምስት አመት? ከአስር አመት? መነሻው ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ መነሻውን ለማስቀመጥ ከዳኛ ዳኛ ሊለያይ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ(context) ውስጥ ወጥነትንና ሚዛናዊነትን ማረጋገጥ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

በቀጣይነት ህጉ እንደሚያዘው ተግባራዊ መደረግ ያለበት የቅጣት ማክበጃዎች ከቀረቡ፣ በቀረቡት ማክበጃዎች መሰረት ቅጣቱን ማክበድ ነው፡፡ ይሁንና ሁሉም ማክበጃዎች ተሟልተው በሚገኙ ጊዜ መድረሻው መሆን ያለበት የትኛው ነው? ለወንጀሉ የተቀመጠው ጣሪያ ነው? በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ውስጥ የሚወድቁ ወንጀሎች ቢሆኑም አንዱ ከሌላው የሚበላለጥ በመሆኑ፣ ለሁሉም ተመሳሳይ ጣሪያ ላይ መድረስ ተገቢ ነው? አንድ ማክበጃ ብቻ ቢሆን መድረሻው የት ነው? ሁለት ማክበጃ ቢኖር መድረሻው የት ነው? ወዘተ፡፡ እነዚህም ለዳኛው ህሊናዊ ዳኝነት የተተዉ ናቸው፡፡

---

[2] የወንጀል ህግ ቁጥር 189

ማቅለያ ምክንያቶቹንም በተመለከተ ቅጣቱ ሲቀል መድረሻው በጥቅሉ ነው የተቀመጠው፡፡ ለምሳሌ ከአንድ አመት በላይ በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ቅጣቶች ቅጣቱ ሲቀል መነሻው አንድ አመት እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ ከአንድ አመት በላይ የጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ያላቸው ለምሳሌ መነሻቸው 3 አመት፣ 5 አመት፣ 7 አመት፣ 10 አመት፣ 15 አመት የሚሉ አሉ፡፡ ስለሆነም ከየትኛው ተነስቶ ነው አንድ አመት ላይ የሚደረሰው? በየደረጃው ላለው የወንጀል አይነት መድረሻው መሆን ያለበት ስንት ነው? ለእነዚህም ህጉ የሚያስቀምጠው መልስ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር በዳኞች መካከል ተመሳሳይና ተቀራራቢ ናቸው በሚባሉ ወንጀሎች የተለያየና የተራራቀ የቅጣት ውሳኔዎች ቢሰጡ የሚገርም አይደለም፡፡

ህጉ ያለበትን ችግሮች ምናልባትም በአሰራር መፍትሄ ተቀምጦላቸው እንደሆነ በሚል በፍርድ ቤት የሚሰጡ የፍርድ ውሳኔዎችን ስንመለከት ችግሮቹ ተባብሶ እናየዋለን፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰንን ወጥነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥናት ያሰራ ሲሆን፣ ለጥናቱ ከተሰባሰቡት የውሳኔ መዝገቦች መረዳት እንደሚቻለው ልምዳችን ህጉን የማይከተል መሆኑን የሚያስረዳ የባሰ ሁኔታ ላይ እንዳለን የሚያመለክት ነው፡፡ የስነስርአት ህጉ እንዳስቀመጠውና በልምድ እንደሚታወቀው አቃቤ ህግና ተከሳሽ ወይም ጠበቃው የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡ እነዚህን አስተያየቶች ስንመለከት ምን ያህል በህጉ ከታሰበውና ከታቀደው የራቅን መሆናችንን መረዳት እንችላለን፡፡

በአቃቤ ህግ የሚቀርቡ የቅጣት አስተያየቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ሪከርድ ስላለበት ቅጣቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ለወንጀለኛውና ለህዝብ ትምህርት የሚሰጥ ቅጣት ይወሰን፣
- በተከሰሰበት ቁጥር ያለው ቅጣት ተመጣጣኝ ይወሰን፣
- ከተሰጠው ሀላፊነትና አደራ አንጻር ትምህርት የሚሰጥ ቅጣት ይወሰን፣
- ሆን ብሎ ከህግ ሸሽተ በማምለጡ ተገቢው ቅጣት ይሰጠው፣
- ከፍተኛ የመንግስት ሀብት የመዘበረ በመሆኑ ከብዶ ይቀጣ፣
- በአፍቅሮ ንዋይ የሰራ ስለሆነ ቅጣቱ ይክበድ፣
- ካደረሰው ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጠው፣
- በስግብግብነት በመስራቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ሪከርድ ስለሌለበት ተገቢው ቅጣት ይሰጠው፣

- ድርጊቱ አደገኛ ስለሆነ ከብዶ ይወሰን፣

የሚሉ ናቸው፡፡

በተከሳሽ የሚቀርቡት የቅጣት ሀሳቦችም ከሞላ ጎደል የአቃቤ ህጉን የሚመስሉ ናቸው፡፡

- ሪከርድ የሌለው በመሆኑ
- ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድር በመሆኑ
- ህብረተሰቡ ውስጥ ጥሩ ጠባይ ስላለው
- ጥፋተኛ የሆኑት ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም በመሆኑ፣
- ቤተሰቦች በከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ በመሆኑ፣
- ብቁ ትምህርት የሌለው በመሆኑ
- የደከሙ እናት አለው
- በመንግስት ስራ ብዙ ያገለገለ በመሆኑ
- በወጣትነት የእድሜ ክልል የሚገኙ ስለሆነ
- ተፈርዶብኝ በእስር ላይ የምገኝ ስለሆነ
- በእስር ላይ በቆየሁበት ጊዜ ተምሬያለሁ
- ከመንግስት ስራ ሌላ መተዳደሪያ የለኝም፡፡

እነዚህ አጠቃላይ ምክንያቶች ዳኛውን ቅጣት ለመወሰን አንዳንድ ነገር ያመለክቱት ካልሆነ በስተቀር ለቅጣት አወሳሰኑ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚቻሉ አይደሉም፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከተው ዳኞች በዚህ መልኩ ተገቢው ርዳታ ሳይቀርብላቸው ነው የሚወስኑት፡፡

ዳኞቹ ቅጣት ሲወስኑስ እንዴት ነው የሚወስኑት?

<u>ቅጣትን ለማክበድ</u>

- የወንጀል ሪከርድ አለው
- የወንጀል አፈጻጸሙ አደገኛ ነው፡፡
- በወስላታነት የተፈጸመ ነው፡፡
- ወንጀል የተፈጸመው አስቀድሞ ዝግጅት ተደርጎበት በመሆኑ አደገኛነቱን ያሳያል
- ስልጣኑንም አለአግባብ በመጠቀም በመሆኑ የአፈጻጸሙን አደገኛነት ያሳያል
- በተሳትፎ ደረጃም ሌሎችን በማሳተፍ በመምራት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡
- ድርጊቱ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ በመሆኑ፣
- በትምህርት የዳበረና ክፉና ደጉን በሚገባ የሚያውቅ በመሆኑ

**ቅጣትን ለማቅለል**

- የወንጀል ሪከርድ የለውም ስለሆነም አደገኛ አይደለም፡፡
- የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው
- ታማሚው ማረሚያ ቤት ቢገባ ሞቱ ይፋጠናል
- ብዙ አመት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገለ በመሆኑ፣
- የድርጊቱ አፈጻጸም አደገኛነትን አያሳይም
- የግል ተበዳይ ጉዳት አልደረሰበትም
- አፈጻጸሙ ቀላል ነው፡፡
- ሪከርድ ስላልቀረበበት የቀድሞ ታሪኩ መልካም ነበር፡፡
- ተከሳሽ በጎ አድራጊ በመሆኑ፣
- በጀት እንዳይመለስና ክልሉ እንዲጠቀም ብለው በመሆኑ፣
- ጡረተኛና በእድሜ የገፉ በመሆኑ
- የአስም በሽታ ያለበት በመሆኑ
- ትምህርት የሌላቸውና በቅንነት የተፈጸመ በመሆኑ
- ፍ/ቤት ብዙ በመመላለሳቸው ትምህርት አግኝበተዋል፣
- የማክበጃ ምክንያት ስለሌለ፣ ሪከርድ ስላልቀረበ
- ድርጉቱን ከግንዛቤ ማነስ በተነሳ ፈፅመውታል
- በግል ስሜት እንጂ የግል ጥቅም ለማግኘት ብለው አይደለም፡፡
- እናቱን የሚጦርና ከስራ ተባሮ ዝቅተኛ ስራ በመስራት ላይ መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቷል
- ድርጉቱን ፍትሐዊ ስራ የሰሩ መስሏቸው የፈፀሙት ነው፣
- ድርጊታቸውም ከባድ ባለመሆኑ ቅጣቱ ሊቀል ይገባል

በሚል በጥቅሉ ካስቀመጡ በኋላ ለማክበዱም ሆነ ለማቅለሉ ምን ያህል እንደጨመሩም ሆነ እንደቀነሱ ሳያስቀምጡ፣ የትኛውን መስፈርት እንደሚጠቀሙ ሳይገልጹ በጥቅሉ የግራ ቀኙን ሀሳብ አገናዝበን የሚከተለውን ቅጣት ሰጥተናል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸውን መዝገቦች ስንመለከት፣

- በአጠቃላይ ቅጣቱን ለመወሰን መነሻው ስንት መሆን እንዳለበት ተመልክቶ አናገኝም፡፡

- በማክበጃነት የቀረቡትንና በማቅለያነት የቀረቡትን ምክንያቶች የሚቀበለውና የሚቀበሉትንና የማይቀበሉትን ከለዩ በኋላ፣ ከምክንያቶቹ ጋር ግንኙነቱን ለማስረዳት በማይቻል መልኩ በጥቅሉ የቅጣቱ መጠን ይቀመጣል፡፡

ስለሆነም፣

- መነሻ የቅጣት መጠኑ ስንት እንደሆነ፣
- በማክበጃነት የተቀመጡት ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድ ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም ማቅለያ ምክንያቶች እንዴት አገልግለው ቅጣቱ እንደቀለለ

ለማወቅ አይቻልም፡፡

በአጭሩ ቅጣቱን ለመወሰን በቀረቡት ምክንያቶችና በተወሰነው ቅጣት መካከል ያለው ምክንያታዊ ግንኙነትን ለማስረዳት የሚያስችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ተሞክሮአችንም ቢሆን በቅጣት አወሳሰን ምንም ስርአት የሌለውና የታቀደለትን ግብና አላማ ያሳካል ለማለት የማይቻል ነው፡፡

__*የመወያያ ጥያቄዎች*__፡-

1. ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ ቅጣትን ለመወሰን ሊደረግ የሚችለው የክርክር ሂደት አስፈላጊነቱንና እስከምን ድረስ እንደሆነ ተወያዩበት፡፡
2. ጥፋተኛነትን ለመወሰን በፍርድ ቤቶች እና በተከራካሪዎች የሚሰጠውን ትኩረት ያክል ቅጣትን በመጣል ላይ ተገቢው ትኩረት አይሰጥም፡፡ ይህ በተለይ የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማዎች ከማሳካት አንጻር እንዴት ይታያል?
3. በቅጣት አወሳሰን ጊዜ ፖሊስ (የወንጀል ምርመራውን ያደረገው አካል)፣ ዐቃቤ ሕግ እና ፍርድ ቤት ያላቸው ሚና ምን እንደሆነ ተወያዩበት፡፡
4. ለቅጣት አወሳሰን ከግራ ቀኙ የሚሰጡ አስተያየቶች ሀሰት ሆነው ቢገኙ የሚያስከትሉት ውጤት ምንድነው? ተከሣሹ ያቀረበው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሀሰት ሆኖ ቢገኝ እንደ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድበት ይችላል? ወንጀል እንደፈፀመ ሊቆጠር ይችላል?

## 6. የቅጣት አወሳሰን የታሰበውን ግብና አላማ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ተግባራት፣

በህጉ ላይ በግልጽ ተገልጾ ባይቀመጥም፣ አጠቃላይ ከቅጣት አወሳሰን ጋር ያለውን የህጉን አቀራረጽ ስንመለከት ቅጣቱን ለመወሰን የሚከተለውን ቅደም ተከተል መከተል እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡ ምክንያቱም ከወንጀል ህጉ ቁጥር 189(1) እንደምንረዳው ዳኛው በመጀመሪያ የቅጣት ማክበጃዎችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ያከብዳል ስለሚል፣ ቅጣቱን ከማክበድ በፊት መነሻ ቅጣቱ ሊወሰን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቅደም ተከተሉ የሚከተለውን ይመስላል ማለት ይቻላል፡፡

1. መነሻ ቅጣትን ያስቀምጣል፡፡ (መነሻ ቅጣቱን ሲያስቀምጥ ደጋጋሚ ከሆነ አክብዶ መነሻ ቅጣቱን ያስቀምጣል)
2. ተከሳሹ ከአንድ በላይ በሆነ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከሆነ ለእያንዳንዱ መነሻ ቅጣት ያስቀምጥና ይደምረዋል፡፡
3. በማክበጃነት የተቀበላቸው ምክንያቶች ከአሉ፣ እነዚህን ምክንያቶች በማስቀመጥ ቅጣቱን በምን ያህል ሊያከብዱ እንደሚገባ ምክንያቶችን አስቀምጦ ቅጣቱን አክብዶ ይወስናል፡፡
4. በማቅለያነት የተቀበላቸው ምክንያቶች ከአሉ፣ እነዚህን ምክንያቶች በማስቀመጥ ቅጣቱን በምን ያህል ሊያቀሉ እንደሚገባ ምክንያቶችን አስቀምጦ ቅጣቱን ያቀላል፡፡

በዚህ መሰረት ደምሮ፣ ጨምሮ፣ ቀንሶ በመጨረሻ የሚደርስበት ለወንጀለኛው የሚወሰንበት ቅጣት ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይሁንና በዚህ መልኩም ቢሰራ እያንዳንዱ ዳኛ መነሻ ቅጣቱንም ሆነ እያንዳንዱ ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያት ሊያስጨምር ወይም ሊያስቀንስ የሚችለውን መጠን ሊወስን የሚችለው በራሱ መመዘኛና መስፈርት ስለሚሆን፣ በተለያዩ ዳኞች መካከል በሚወሰኑ ውሳኔዎች መካከል ወጥነት ያለመኖር መከሰቱ አይቀርም፡፡ ከዚህ አንጻር ዳኞች ተመሳሳይ መስፈርቶች እንዲኖራቸው የሚያደርግ ዝርዝር መመሪያ መኖሩ በቅጣት አወሳሰን ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት ዘላቂ መፍትሄ ነው፡፡ ይህንንም ችግር ከግምት በማስገባት በወንጀል ህጉ ቁጥር 88(4) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የቅጣት አወሳሰን ወጥነትና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንደሚያወጣ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረትም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የቅጣት አወሳሰን ለማውጣት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ ይሁንና የቅጣት አወሳሰን

መመሪያ እስከሚወጣ ድረስ አቃቤ ህጎችም ሆኑ ዳኞች ለቅጣት አወሳሰን በህጉ የተመለከቱትን መመሪያዎች መሰረት አድርገው ለመወሰን ጥረት ቢያደርጉ አሁን ካለው የቅጣት አወሳሰን ችግር በእጅጉ የተሻለ አሰራር ሊኖር እንደሚችል ግን መገመት አያዳግትም።

## ዋቢ ሰነዶች፣


1. የወንጀል ህግ 1996፣
2. የተለያዩ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች
3. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፕሪዝን ፌሎውሺፕ በጋራ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለማዘጋጀት የተዘጋጁ ረቂቅ ጥናቶች (2001)